# ኮቪድ-19 በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የአልባሳት አቅርቦት ሰንሰለቶች ላይ ያደረሰው አቻ የሌላቸው ተጽዕኖዎች፡-

## ከኢትዮጵያ ፣ ከሆንዱራስ ፣ ከህንድ እና ከማይናማር በተገኙ መረጃዎች መሰረት


**Authored by**

Genevieve LeBaron

Penelope Kyritsis

Perla Polanco Leal

Michael Marshall



The University Of Sheffield.

Department Of Politics & International Relations.

speri.

WRC

WORKER RIGHTS CONSORTIUM

# ዋና ማጠቃለያ

## ስለ ሪፖርቱ

ይህ ሪፖርት በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ በልብስ አቅርቦት ሰንሰለቶች ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች የኑሮ እና የሥራ ሁኔታ ችግር መባባሱን እንዲሁም ለጉልበት ሥራ ተጋላጭነታቸው እስጊ በሆነ ሁኔታ መጨመሩን ያሳያል።

ይህን ጥናት ያካሄድነው የዓለም አቀፉ የአልባሳት አቅርቦት ሰንሰለት ንግድ እንዲሁም ሰራተኞቻቸው ወረርሽኙ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳደረሰባቸው ለመመርመር ነው። ይህም ጥናት በአራት አልባሳት አምራች እና ላኪ በሆኑ ሀገራት ላይ በሚገኙ ሰራተኞች ላይ ያተኩራል። እነዚህም ሀገራት ኢትዮጵያ ፣ ሆንዱራስ ፣ ህንድ እና ማያንማር ናቸው። ሀገራቱ በእንግሊዝ ፣ በአሜሪካ ፣ በአውሮፓ ፣ በካናዳ እንዲሁም በተለያዩ ሀገራት ውስጥ ላሉ የልብስ ብራንዶች እና ሸማቾች ዋነኛ የአልባሳት አቅራቢዎች ናቸው። ጥናቱ ከዘመናዊ ባርነት እና ሰብአዊ መብቶች ፖሊሲ እና መረጃ ማዕከል (Modern Slavery and Human Rights Policy and Evidence Centre) በተገኘ ድጋፍ ከጥቅምት እስከ ግንቦት 2013 ዓ.ም ተካሂዷል።

በወረርሽኝ ወቅት የምርምር ስራ ማካሄድ የራሱ የሆኑ ተግዳሮቶች መኖራችው በስራ ሁኔታዎች ላይ የደረሰውን ተጽዕኖ የሚያሳይ መረጃ ከሰራተኞች በተገኙ ማስታወሻዎች እንዲወሰን እና አጠቃላይ የማስረጃዎችን ብዛት አናሳ እንዲሆን አድርጎታል። ይህም ሰፋፊ ጥናቶችን ለማድረግ የሚጋብዝ ሆኖ አልተገኘም። ኮቪድ 19 በአልባሳት አቅርቦት ሰንሰለቶች ላይ ያደረሰውን ተጽዕኖ ያጠኑ ምርምሮች የሰንሰለቱ ዋና አካላት የሆኑትን ሰራተኞች ድምጽ በመተው ከድርጅቶች በተገኘ መረጃ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

ስለዚህም ይህ ጥናት በተቃራኒው በመመልከት ምርምሩን ያደረገው በወረርሹኙ ወቅት ስራ ላይ በነበሩ እንዲሁም በወረርሽኙ ምክንያት የስራ ውል ስምምነታቸው በተቋረጠባቸው ሰራተኞች ላይ ነው። የምርምራችን ዋነኛ ትኩረት የኑሮና የሥራ ሁኔታ አመልካቾች የሆኑት የሥራ ዋስትና ፣ የገቢ መጠን ፣ ለጉልበት ሥራ ተጋላጭነት እና  ዕዳ በወረርሽኙ ምክንያት እንዴት እንደተለወጡ መመርመር ነው። ይህንንም ለመመርመር ሰፊ የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት አካሂደናል። ጥናቱም በተለያዩ ሀገራት ከሚገኙ ሰራተኞች እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ ዳሰሳዊ ጥናቶች እንዲሁም ቃለ መጠይቆች ላይ የተደገፈ ነው። በኢትዮጵያ ፣ በሆንዱራስ ፣ በሕንድ እና በማያንማር ከሚገኙ 1140 ሰራተኞች ላይ ዲጅታል የዳሰሳ ጥናት ተሰብስቦል፤ በኢትዮጵያ ፣ በሆንዱራስ ፣ በሕንድ ከሚገኙ 60 ሰራተኞች ጋር ቃለ መጠይቆች ተደርጎዋል፤ 20 ከሚሆኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተወካዮች ጋር ቃለ መጠይቆች ተደርጎዋል። እነዚህም ተወካዮች ከተለያዩ የልብስ ብራንዶች፣  ከመንግስት፣ ከማህበራዊ ተገዢነት ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች እና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተውጣጡ ናቸው፤ የ21 የአልባሳት ኩባንያዎችን የ2013 ዓ.ም ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎችን እና የዘላቂነት ሪፖርቶችን ያጠናቀረ የመረጃ ቋት ተፈጥሮዋል።  በተጨማሪም ይህ የመረጃ ቋት  የካናዳ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሆንዱራስ ፣ ህንድ ፣ ማያንማር ፣ እንግሊዝ እና አሜሪካ መንግስታት በወረርሽኙ ወቅት የንግድ ዘርፉን ለመደገፍ የነደፏቸውን ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርቶች ይዟል።

ይህ ሪፖርት በዋነኝነት የሚያተኩረው በሰራተኞች ደረጃ ባለ መረጃ ላይ ሲሆን ይህም የሆነው እስከ አሁን የተደረጉ ተመሳሳይ ምርምሮች የሰራተኛውን ድምፅ እና ምልከታ ያላካተቱ በመሆናቸው ነው።

## የጥናቱ ግኝቶች ማጠቃለያ

ጥናታችን የልብስ ሰራተኞች የስራ እና የኑሮ ሁኔታ ችግር በወረርሽኙ ወቅት በጣም መባባሱን ያሳያል። ጥናቱን ባካሄድንባቸው በአራቱም ሀገራት የሚገኙ ሰራተኞች ለጉልበት ሥራ ቁልፍ አመልካቾች ተጋላጭነታቸው ከመጨመሩም በላይ በገቢያቸው እና በሥራ ሁኔታቸው ላይ ከፍተኛ ማሽቆልቆል ደርሶባቸዋል፡ ፡ እነዚህ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች በሥራ ቅጥራቸው ሁኔታ ላይ ምንም ለውጥ ሳይኖርባቸው በተመሳሳይ ሥራ ላይ ለቆዩ ሠራተኞች እንዲሁም በወረርሽኙ ወቅት የሥራ ውላቸው ለተቋረጠ እና አዲስ ሥራ ባላገኙ ሰራተኞች ላይ ታይቶል። በሥራ ውላቸው መቋረጥ ምክንያት አዲስ ሥራ ያገኙት ሰራተኞች ከወረርሽኙ በፊት ከነበረቸው ቅጥር ጋር ሲነፃጸር ዝቅተኛ ደመወዝ እና የከፋ የሥራ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህ ምልክቶች ጥናቱ በተደረገባቸው ሀገሮች፤ በግለሰቦች መካከል ባሉ የዕድሜ ፣ የጾታ ፣ የዘር እና የጎሳ ልዩነቶች፤ ከማህበራት ጋር ባለ ትስስር፤ የቅጥር ሁኔታ፤ ፍልሰት እንዲሁም የንግድ ተለዋዋጭነት አንፃር ልዩነት አሳይተዋል።

### የሥራ ዋስትና

— በጥናታችን ውስጥ ከተሳተፉት 1140 ሠራተኞች መካከል፣ 72 በመቶ የሚሆኑት በወረርሽኙ ወቅት ሲሰሩ በነበሩት ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥረው የቆዩ ሲሆኑ 17 በመቶው ደግሞ ሌላ ሥራ አግኝተዋል። ቀሪዎቹ 11 በመቶ ግን በአሁኑ ጊዜ ስራ የላቸውም ።

— ከሠራተኞቹ 13 በመቶ የሚሆኑት ከወረርሽኙ በፊት የነበራቸው የሰራ ውል ተቋርጧል።ይህ  በወረርሽኙ ጊዜ ለብዙ ሰራተኞች ስራ መቀየር እንዲሁም ማጣት ዋነኛ ምክንያት ነበር። ከእነዚህ ሠራተኞች መካከል 80 በመቶ ያህሉ ሙሉ የአገልግሎት ክፍያ አልተከፈላቸውም። ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት ደግሞ ምንም አይነት ክፍያ  አልተከፍላችውም ።

— በአናሳ ብሄር ወይም ጎሳ ውስጥ ያሉ ሰራተኞች የሰራ ውላቸው የመቋረጡ እድል ሰፊ ሆኖ ሲገኝ በተቃራኒው በማህበራት ውስጥ የተካተቱ ሰራተኞች የሥራ ውል ስምምነታቸው የመቋረጥ ዕድሉ አናሳ ሆኖ አግኝተነዋል ።

# 80 በመቶ ያህሉ ሰራተኞች ሙሉ የሥራ ሰንብት ደመወዝ አልተከፈላቸውም፡፡ ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት ደግሞ ምንም አይነት ክፍያ አላገኙም፡፡

## ደመወዝ እና የሥራ ሁኔታ

— አሁን ካሉት ሰራተኞች መካከል የአማካይ ወርሃዊ ገቢ ከወረርሽኙ በፊት ከነበርው 627.45 ዶላር ወደ 560.36 ዶላር ወርዷል ፡፡ በሌላ አገላለጽ ሠራተኞቹ ወርሃዊ ገቢያቸው በአማካይ በ11 በመቶ ቀንሷል ፡፡ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተጠቀሱት የገንዘብ መጠኖች ጠቅላላ በአሜሪካ ዶላር የምንዛሬ ተመን ሳይሆን በገንዘብ የግዢ ኃይል እኩልነት የተገለጹ ናቸው ፡፡ ይህም በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተጠቀሱት የሰራተኛ ገቢ አኃዞች ከቀዳሚው የWRC ህትመቶች የበለጠ ከፍ ያሉ ያስመስላቸዋል፡፡

— በወረርሽኙ ወቅት ሰራተኞች ለጉልበት ሥራ መጋለጣቸውን የሚያሳዩ ቁልፍ አመላካቾች ጨምረው ተገኝተዋል ፡፡ አሁን በሰራ ገበታ ላይ ከሚገኙት መላሾች መካከል 356 ሰራተኞች (35%) የቃላት ጥቃት እንደ ደረሰባቸው፣ 245 ሰራተኞች (34%) ማስፈራሪያ እንደ ደረሰባቸው ፣ 224 ሰራተኞች (22%) ደግሞ ፍትሀዊ ያልሆነ የደመወዝ ቅነሳ ወይም እገዳ እንደተደረገባቸው ፣ ቀሪዎቹ 196 ሰራተኞች (19%) ደግሞ እንደ ውሃ እና መጸዳጃ ያሉ መሰረታዊ ነገሮችን እንዳያገኙ መከልከላቸውን ገልጸዋል፡፡ ለአብዛኞቹ መላሾች እነዚህ ሁኔታዎች ከወረርሽኙ በፊት ያልነበሩ ተሞክሮዎች እና አዲስ የሆነባቸው ሲሆን ለሌሎች ደግሞ እነዚህ ችግሮች ከወረርሽኙም በፊትም የነበሩ ቢሆኑም የዚህን ያክል የተሰፋፉ ወይም የከፉ አልነበረም፡፡

— ከመላሾቹ መካከል 399 ሰራተኞች (39%) የሚሆኑት የግል መከላከያ መሳሪያዎች (PPE) እጥረት እንደነበረ እና ማህበራዊ መራራቅ አለመኖሩን ገልፀዋል ፡፡

— በወረርሽኙ ወቅት ሥራ ከቀየሩ ሠራተኞች መካከል ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት በአዲሱ ሥራቸው ላይ የከፋ የሥራ ሁኔታ እንደገጠማቸው ተናግረዋል ፡፡ ከጠቀሷቸው ችግሮች መካከል ዝቅተኛ የደመወዝ መጠን ፣ አነስተኛ የሥራ ዋስትና እና ለበለጠ አደጋ እና ስጋት ላይ መውደቃቸውን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ሥራቸውን ከቀየሩ ሠራተኞች መካከል 68 በመቶ ያህሉ ምንም አይነት የጽሑፍም ሆነ የቃል የሰራ ውል አልነበራቸዉም ፡፡ ከአዲሱ ሥራቸው የሰራ ውል ስምምነት ከተቀበሉ ሠራተኞች መካከል ደግሞ 19 በመቶ የሚያህሉት ሰራተኞች የአዲሱ ስምምነት ውል ቀድሞ ከነበራቸው ውል የከፋ እንደሆነ ገልፃዋል፡፡

## የሰራተኛ ዕዳ

— ሰራተኞች እንደ ምግብ ፣ ቤት ፣ ሕክምና ያሉ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ሲሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ በእዳ ውስጥ እየተዘፈቁ መጥተዋል፡፡ እነዚህም የኑሮ እና የሰራ ሁኔታዎችን የሚቀርጹ ዋና አመልካቾች ናቸው፡፡ በወረርሽኙ ወቅት ሠራተኞች መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚያስችል በቂ ደመወዝ አልነበራቸውም፡፡ በተጨማሪም ከመንግሥት እና ከሲቪል ማኅበራት የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ተቸግረዋል ፡፡

— በቤተሰብ ደረጃ አማካይ የእዳ መጠን ከወረርሽኙ በፊት ከነበረው አማካይ 1835.23 ዶላር ወደ 2125.48 ዶላር ያህል አድጓል፡፡ ይህም 16 በመቶ ጭማሪ ያሳያል ፡፡ በኢትዮጵያ አማካይ የቤተሰብ ደረጃ የእዳ መጠን ከእጥፍ በላይ አድጓል ፡፡ በማየናማር በ 34 በመቶ ፣ በሕንድ 21 በመቶ እና በሆንዱራስ በ 6 በመቶ አድጓዋል ፡፡

— ከ 60 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሠራተኞች በወረርሽኙ ወቅት ብድር ተበድረዋል፡፡ የብድር መጠናቸው መረጃ ካለን ከ1083 ሰራተኞች መካከል 451 (42 በመቶ) የሚሆኑት ሰራተኞች የእዳቸው መጠን ሲጨምር ተመልክተዋል ፡፡ በወረርሽኙ ወቅት ተጨማሪ ዕዳን መውሰድ ከከፍተኛ ጉልበት ሥራ ተጋላጭነት ጋር ትልቅ ተያያዥነት እንዳለው ተስተውሏል፡፡

— በጥናታችን ውስጥ ከተካተቱት አብዛኛዎቹ ሠራተኞች በወረርሽኙ መጀመሪያ ላይ ምንም አይነት ቁጠባ አልነበራቸውም ፡፡ ቁጠባ የነበራቸው ሰራተኞች ደግሞ አማካይ ቁጠባ በወረርሽኙ ወቅት ወርዷል፡፡ ይህም ከወረርሽኙ በፊት ከነበርው አማካይ 409.18 ወደ 136.71 ዶላር ቀንሶ ታይቷል፡፡ ምንም ቁጠባ የሌላቸው መላሾች ጠቅላላ ብዛት በ 25 በመቶ አድጓል ፡፡

## የንግድ እና የመንግስት ምላሾች

— በአቅርቦት ሰንሰለቱ አናት ላይ የሚገኙ ዓለም አቀፍ የልብስ ኮርፕሬሽኖች ማለትም የፋሽን ብራንዶች እና ቸርቻሪዎች - በወረርሽኙ ወቅት የተለያዩ የንግድ ውጤቶች አግኝተዋል ፡፡ አንዳንዶቹ ከወረርሽኙ በፊት በነበሩት ዓመታት ጋር ሲነፃፀሩ ዝቅተኛ ትርፍ ሲያጋጥማቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ሽያጫቸው እንዲሁም የብር መጠናቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ፡፡

— ከኢንዱስትሪ ተወካዮች ጋር ያደረግነው ቃለ-መጠይቅ፣ ዓለም አቀፍ የልብሰ ኮርፕሬሽኖች በወረርሽኙ ወቅት የተለያዩ የንግድ ውጤቶች ቢያገኙም በወረርሽኙ መጀመርያ ላይ ግን አብዛኞቹ ኮርፕሬሽኖች ማህበራዊ ግዴታቸውን ከመወጣት ይልቅ ትርፋቸውን በማስቀደም እና ያላቸውን ያልተመጣጠነ ሀይል፣ መልካ-ምድራዊ እና የህግ-መዓቀፍ ርቀት በመጠቀም ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳት እና ኪሳራ፣ ይሄን ጫና የመሸከም አቅም ወደ ሌላቸው አቅራቢዎቻቸው እና ሰራተኞቻቸው ላይ ማዘዋወራቸውን ያሳያል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ጥቂት የሚባሉ ዓለም አቀፍ የልብሰ ኮርፕሬሽኖች ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ ለወረርሽኙ ምላሽ ሰተዋል፡፡ እነዚህ ኮርፕሬሽኖች አብዛኛዎቹ በባለቤትነት የተያዙ ወይም ደግሞ ከፍተኛ የተከማቸ አቅርቦት መሰረት መሆናቸው ኮርፕሬሽኖች የነበራቸውን ይህን የንግድ መሰክ እና የቆየ የንግድ ግንኙነቶች እንዲጠብቁ አበረታቷቸዋል፡፡

- በወረርሽኙ መጀመርያ ላይ የዓለም አቀፍ የልብስ ኮርፕሬሽኖች ሀላፊነት ያልተሞላበት ምላሽ በአቅርቦት ሰንሰለቱ ላይ ተከታታይ የሆኑ ጉዳቶችን አድርሷል ። ከነዚህም ጉዳቶች መካከል አቅራቢዎች ለጊዜው ወይም ላልተወሰነ ጊዜ እንዲዘጉ ምክንያት ሆኗል። ይህም ብዙ ሠራተኞች ከሥራ እንዲሰናበቱ፣ የስራ ክፍያ እንዲያንስ እንዲሁም ለጉልበት ስራ ተጋላጭነታቸው እንዲጨምራል አድርጓል። በወረርሽኙ እኩሌታ አካባቢ አንዳንድ የልብስ ኮርፕሬሽኖች ወረርሽኙ ያደረሰባቸውን ጉዳት ለመጠገን ሞክረዋል። ይህንንም ለማሳካት ለአቅራቢዎቻቸው የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ፣ ቅድመ ክፍያዎችን በመስጠት እና የመጫኛ እና የማስረከቢያ ጊዜዎችን በማላላት ወረርሹ ያመጣውን ጉዳት ለመቀነስ ሞክረዋል። ሆኖም ግን አሁንም ዋናዎቹ ችግሮች አልተቀረፉም ።
- በመንግሥትም ሆነ በግል የአቅርቦት ሰንሰለት ዓይነቶች ላይ የአስተዳደር ብልሽት ታይቷል ። መንግስትም ሆነ የዓለም አቀፍ የልብስ ኮርፕሬሽኖች የስራተኛ መለኪያ መስፈርቶችን ማስፈፀም ባለመቻላቸው ሰራተኞቻቸው አነስተኛ ጥበቃ እንዲኖራቸው ሲያደርግ ቀጣሪዎቻቸው ደግሞ የስራ ደረጃውን ለማውረድ አስችሏቸዋል።
- ወረርሽኙ በልብስ አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ቋሚ ኢ-ፍትሃዊ የሆኑ ድርጊቶች እንደ የእሴት ክፍፍል፣ በባለድርሻ አካላት መካከል ያለ የኃይል ልዩነት እንዲሁም ሰራተኞች እና ድርጅቶቻቸውን ያገለለ የአስተዳደር ስርዓቶችን በፍጥነት እያጎላቸው ይገኛል።

## ወረርሽኙ ጊዜያዊ ችግሮችን ከማባባሱም በላይ በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ቋሚ ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶችን በፍጥነት እያጎላቸው ይገኛል።